## የ COLUMBIA አውራጃ ከፍተኛ ፍርድቤት

የፍትሀብሔር መምሪያ፣ የአከራይ እና ተከራይቅርንጫፍ

የፍርድቤት ህንጻ B, 510 4 መንገድ, NW, RM. 110 Washington, DC 20001 ስልክ(202) 879-4879

Instructions for Serving Summons and Complaint for Landlord & Tenant

### የአከራይ እና ተከራይመጥሪያዎች እና ማመልከቻ የማድረስ መመሪያዎች

የሚያደርሰው ማን ነው: የአከራይ እና ተከራይ(L&T) መጥሪያዎች እና ማመልከቻ እንዲሁም አባሪዎቹ መድረስ ያለበት ቢያንስ 18 አመት በሞላው እና ለጉዳዩ ተከራካሪ ወገን ባልሆነ ሰው ነው::

የማድረስ ቃለ-መሀላ: የቃለ-መሀላ ቅጾች በጸሀፊ ጽ/ቤት ይገኛሉ:: መጥሪያውን እና ማመልከቻውን የሚያደርሰው ሰው ቃለ-መሀላ መፈረም አለበት:: የተሞላው ቃለ-መሀላ በክብር መዝገብ ሹመኛ ወይም ሌላ በሀላ ለማስደረግ በህግ የተፈቀደለት ሰው ፊት መሀላ ተደርጎበት ከመጀመሪያው የአቤቱታ መስሚያ ቀን በፊት ቢያንስ 5 ቀናት ቀደም ብሎ ማለትም ቅዳሜ፣ እሁድ እና ህጋዊ የበአል ቀናት ሳይቆጠሩ ፍርድት መግባት አለበት:: ለእያንዳንዱ መልስ ሰጪ የተለየ ቃለ-መሀላ መግባት አለበት::

መቼ እና እንዴት እንደሚደርስ: መድረስ ያለበት ከመጀመሪያው የአቤቱታ መሰሚያ ቀን ከ7 ባልበለጡ ቀናት በፊት ማለትም እሁድ እና ህጋዊ የበአል ቀናት ሳይቆጠሩ መድረስ አለበት:: D.C. Code §16-1502.

የ L&T መጥሪያዎች እና ማመልከቻዎች የሚደርሱበት ሶስት መንገዶች አሉ: 1) በግንባር ማድረስ; 2) በተተኪ ማድረስ; 3) በፖስታ ማድረስ:: ከስር በሚገኙት አንቀጾች በዝርዝር ተገልጿል:: በእያንዳንዱ ጉዳይ አድራሹ መጀመሪያ በግንባር ለማድረስ በቅን ልቦና ጥረት ያደርጋል:: አድራሹ በግንባር ለማድረስ በትጋት እና እስከመጨረሻው ጥረት አድርጎ ለመልስ ሰጪው/ሰራኛው በግንባርም ይሁን በተተኪ አድራሽ ማድረስ ካልቻለ የመጨረሻው አማራጭ በፖስታ መላክ ነው::

የገንዘብ ፍርድ: ከይዞታ ፍርድ በተጨማሪ የገንዘብ ፍርድ ከጠየቁ የገንዘብ ፍርድ ለጠየቁት እያንዳንዱ መልስ ሰጪ/ተከራይ በግንባር ማድረስ አለብዎት:: መልስ ሰጪ/ተከራዩን በግንባር ካላደረሱት በይዞታ ፍርድ ላይ ብቻ ይወሰናሉ::

በግንባር ማድረስ: ግለሰብ ለሆነ መልስ ሰጪ/ተከራይ የሚደርሰው በግንባር ሄዶ የመጥሪያውን እና ማመልከቻውን ቅጂ በመስጠት ነው:: ለመልስ ሰጪው/ተከራይው በግንባር ካደረሱት በቃለ-መሀላው ላይ የመጀመሪያውን ሳጥን ምልክት ያድርጉ:: ያደረሱትን ሰው ስም ቃለ-መሀላው ላይ እንዲጽፉት ባዶ ቦታ ላይ ይጻፉ እንዲሁም በቃለ-መሀላው መጨረሻ ላይ የተለዩ እውነታዎች በሚለው ክፍል ላይ የመልስ ሰጪውን/ተከራዩን አካላዊ መግለጫ ይስጡ::

ተተኪ አድራሽ: መልስ ሰጪውን/ተከራዩን ማግኘት ካልቻሉ ወይም የ Columbia አውራጃን ከለቀቀ የመጥሪያውን እና ማመልከቻውን ቅጂ ቢያንስ 16 አመት የሞላው፣ በቦታው የሚኖር ወይም ቦታውን ይዞ የሚገኝ "ለመወሰን ብቁ" የሆነ ሰው ጋር በመተው ማድረስ ይችላሉ::

በቃለ-መሀላው ላይ ሁለተኛውን ሳጥን ምልክት ያድርጉ:: በቃለ-መሀላው መጨረሻ ላይ የተለዩ እውነታዎች በሚለው ክፍል ላይ የመልስ ሰጪውን/ተከራዩን አካላዊ መግለጫ ይስጡ::

በፖስታ ማድረስ: በፖስታ ማድረስን የሚጠቀሙት መልስ ሰጪውን/ ተከራዩን በግንባር ለማድረስ በትጋት እና እስከመጨረሻው ጥረት አድርጎ ካልተሳካ እንደ መጨረሻ አማራጭ ነው:: በፖስታ መድረሱ ጥያቄ ካስነሳ ዳኛው የጉዳዩን እውነታዎች በማገናዘብ አድራሹ በትጋት እና እስከመጨረሻው ጥረት ማድረጉን ይወስናል:: በአጠቃላይ በትጋት እና እስከመጨረሻው ጥረት ተደርጓል ብሎ ዳኛው የሚወስነው ሙከራዎቹ በሁለት የተለያዩ ቀናት እና በአንድ ቀን በሁለት የተለያዩ ጊዜዎች ከተደረጉ ነው:: ለምሳሌ፡ አንዱ ሙከራ በስራ ቀናት፣ በመደበኛው የስራ ሰአት ከተደረገ ሌላኛው ሙከራ መደረግ ያለበት ቅዳሜ እና እሁድ ከመደበኛው የስራ ሰአት በፊት ወይም በኋላ

በፖስታ ካደረሱ መጥሪያውን እና ማመልከቻውን ጊቢው ላይ በሚታይ ቦታ ላይ፣ በግልጽ ሊነበብ በሚችልበት ቦታ ላይ መለጠፍ አለብዎት፤ ብዙ ጊዜ የፊትለፊት በር ላይ ነው:: መለጠፍ ማለት መጥሪያውን እና ማመልከቻውን ከቦታው ግርግዳ ጋር ማያያዝ ነው:: ወረቀቱን በበር ስር ማስቀመጥ፣ በበሩ እና በበሩ ጠርዝ መካከል ባለው ቀጭን ክፍተት ላይ ማንጠልጠል ወይም የፖስታ ሳጥን ውስጥ ማስቀመጥ አይችሉም:: ከለጠፉ በኋላ የመጥሪያውን እና ማመልከቻውን ቅጂ ለመልስ ሰጪው/ተከራይው በ3 ቀናት ውስጥ መላክ አለብዎት:: ቅዳሜ፣ እሁድ እና ህጋዊ በአላት በ3 ቀናት ውስጥ ይካተታሉ:: በግንባር በማድረስ ወቅት የሁሉንም ሙከራዎች ቀን እና ሰአት የተለጠፈበትን ጨምሮ መመዝገብ አለበት እንዲሁም መጥሪያው እና ማመልከቻው የተላከበት ቀንም መጻፍ አለበት:: በቃለ-መሀላው መጨረሻ ላይ የተለዩ እውነታዎች በሚለው ክፍል ላይ መጥሪያው እና ማመልከቻው የት እንደተለጠፈ፣ የህንጻው የትኛው ቦታ እንደሆነ፣ የቦታው አካላዊ ገለጻ እና/ወይም አደራረሱ አግባብ እንደነበር ለፍርድቤቱ የሚያሳይ ሌላ ማንኛውም መረጃ ይስጡ::

በድርጅት ወይም LLC ማድረስ: በድርጅት ወይም የተወሰነ ሀላፊነት ያለው ኩባንያ (LLC) በኩል ሲደርስ የመጥሪያው እና ማመልከቻው ቅጂ ለፖሊስ፣ ለሀላፊ ወይም አጠቃላይ ወኪል፣ የተመዘገበ ወኪል ወይም ሌላ ሰው በህግ ስለጣን የተሰተው ወይም ለተመደበ ሰው ይሠጣል:: የተመዘገበ ወኪል ከሌለ ለከንቲባው በመስጠት ለድርጅት ወይም LLCው ማድረስ ይቻላል:: መመሪያውን ለማግኘት የተጠቃሚዎች እና አስተዳደር ጉዳዮች መምሪያን ያነጋግሩ:: ለድርጅት ወይም LLC ካደረሱ ቃለ-መሀላው ላይ አራተኛውን ሳጥን ምልክት ያድርጉ:: ያደረሱትን ሰው ስም ባዶ ቦታው ላይ ይጻፉ፣ የሰውየውን ማዕረግ ይጻፉ እና የሰውየውን አካላዊ ገለጻ ወይም ሌላ ጠቃሚ መረጃ በቃለ-መሀላው መጨረሻ ላይ የተለዩ እውነታዎች በሚለው ክፍል ላይ ይስጡ:: ለድርጅቱ ለማድረስ አማራጭ መንገድ ከተጠቀሙ በቃለ-መሀላው ላይ አማራጩን እና ማንኛውም አስፈላጊ እውነታ ይግለጹ::